# በሁሉም ደረጃ ያሉት እድገቶች መቆጣጠር(የአስተዳደር ፍጻሜዎች)

## አጭር መግለጫ

የመንግስት ድርጅቶች፣ ኩባኒያዎች እና አትራፊ ያልሆኑ ድርጅቶች ሁሉ ለመሻሻልና ጥራት ለአለው አሰራር እንዲኖራቸው የሚቻላቸው ሁሉ ጥረት ያደረጋሉ።የሚጠበቅባቸውን ውጤት ለማግኘት እድገታቸውን የሚቆጣጠሩበት አሰራር አላቸው።በችሎታቸው ድክመት ያሳዩትን ተሎ ለይቶ በማወቅ አስፈላጊውን ድጋፍ እንዲያገኙ ማድረግ፣ ከፍተኛ ውጤት የሚያመጡትን ደግሞ በይበልጥ ማበረታታት።እድገትንና ውጤትን የምትቆጣጠርበት አሰራር በሁሉም ደረጃ እንዲኖር ማድረግ በጣም ወሳኝ ነው።

የስያትል ህዝባዊ ትምህርትቤቶች አስተዳደር በሁሉም ትምህርትቤቶች ጥሩ አስተዳደር እንዲኖር እንዲሁም ተጠያቂነትና የአስተዳደር ፍጻሜዎች የሚለካበት አሰራር እንዲኖር ለማድረግ ቆርጦ ተነስተዋል።ዲስትሪክቱ ከሁሉም በላይ ቅድሚያ በመስጠት ይህንን አይነት አሰራር በመጪው ስድስት ወር ውስጥ ስራ ላይ እንዲውል ያደረጋል።

## ዋና አስፈላጊ ነገሮች

በዚህ አመት የበለጠ ትኩረት የሚሰጣቸው አንዳንድ አስፈላጊ ነገሮች አሉን

**አለማ ግልጽ ማድረግ** – ተማሪዎች እንዴት ጥሩ ውጤት ለማምጣት እንደሚችሉን የኛ ተጠያቂነት ምን ሊሆን እንደሚችል በግልጽ ማስቀመጥ።የወደፊት አላማችን አንስተኛ ቁጥር ተማሪዎች ያሉበት ክፍል እንዲኖር ማድረግና ጥሩ የአስተዳደር አሰራር እንዲኖር ማድረግ ነው።

**ማስታወቂያ የሚለጠፍበት ጣውላ ማዘጋጀት** - በየጊዜው የምናደርጋቸው ስራዎችና የተገኙት ውጤቶች አባሎች እንዲያዩት በቦርዱ (ጣውላ) ላይ እንዲለጠፍ ማድረግ።በዚህ መልክ ውጤታችንና የወደፊት አላማችን ለመለካት የሚያስችለን አሰራር ሊኖረን ይችላል።የዚህ አይነት (ጥቁር ሰሌዳ ጣውላ)አሰራር በሁለት ነገሮች ላይ ያተኮረ ይሆናል፣ እነሱም

- በዋናው ጽህፈት ቤት የሚለጠፍ ጥቁር ሰሌዳ ጣውላ – ዋናው ጽህፈት ቤት የሚሰራቸው ስራዎችና ፕላን ምን እንደሆነና በተካሄዱት ውይይቶች የተነሱ ሃሳቦች ምን ምን እንደነበሩ ግልጽ እንዲሆኑ ማድረግ።ይህ ሰዎስት የተለያዩ ዲፓርትመንቶች መጥቀስ ይቻላል ለምሳሌ (የሂሳብ ክፍል፣ የቴክኖሎጂን ፔርሰናል ክፍል) እነዲሁም አካዳሚክ ክፍል
- የዋና ስራ አስከያጁ ጥቁር ሰሌዳ ጣውላ – ዋና ስራ አስከያጁ ስራ ላይ እንዲውሉ ቅድሚ የሰጣቸው ስራዎች ምንና ምን እንደሆኑ የተገኙት እድገቶች ምን እንደሆኑ ግልጽ እንዲሆኑ ማድረግ።

**የትምህርትቤቶች እድገት የሚለካበት አሰራር እንዲኖር ማድረግ** – በዚህ መልክ የእያንዳንዱ ትምህርትቤት የሚያስመዘግቡት የአካዳሚክ ውጤታቸው የሚለካበት አስራር እንዲኖር በማድረግ ድክመት የሚያሱ ትምህርትቤቶች ካሉም በጊዜው አስፈላጊውን ድጋፍና እርዳታ እንዲያገኙ ማድረግ።ይህ አሰራር በዚሁ አመት ማለት በ2008 መጨረሻ አካባቢ ላይ እንዲነደፍ ይደረግና በ09-10 የትምህርት ዘመን ሙሉ በሙሉ ስራ ላይ እንዲውል ይደረጋል።

## ለህብረተሰቡ የሚቀርቡ ጥያቄዎች

- በይበልጥ ለማወቅ የምትፈልጉት ነገር ምንድነው?
- ግልጽ ያልሆነላችሁ ነገር ካለ?
- የጎደለ ነገር ካለ?
- ስለ አሰራራችን ያሉት መረጃዎች ሁሉ በምን መንገድ እንዲደርሳችሁ ትፈልጋላችሁ?